# የምፅዐቱ የምሥራች

ቅፅ 66 ቁጥር 3(783) "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ::" (ሐዋ 1÷8)

## መንፈስ ቅዱስ፣ በአለ ሃምሳ ወይም ጰንጠ ቆስጤ ኢየሩሳሌምን አናውጧል

ጌታ በበአለሃምሳ ወይም በጰንጠ ቆስጤ ዕለት እየሩሳሌምን እንዳናወጠ ሁሉ ዛሬም መንፈስ ቅዱስ ሊያነቃቃን እግዚአብሔር ሰራውን ጀምሯል::

በበአለሃምሳው ዕለት ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደእሣት ነበልባል የሰዎችን ኃጢአት ከሚያቀልጥ የተቀባ ንግግር ሌላ አልተናገረም::

«የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬት ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ታምራትና በድንቅ በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር:: እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞቹ እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት:: እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለም» (ሐዋ 2÷22)::

### በኃጢያት መፀፀት

«ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ? አሉዋቸው» (ሐዋ 2÷37)

### ንስኃ

«ጴጥሮስም ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ የተስፋው ቃል ጌታ አምላክ ለሚጠራቸው ሁሉ ነው»::

### የዛሬው ለብታ

በዛሬው ዘመን ጐልተው በመንፈሳውያን መካከል ከሚታዩት ኃጢአቶች ዋነኛው ይህ ጉዳይ ሲሆን ታማኝና ታታሪ የእግዚአብሔር ሰዎች የጐደለባቸውን የልብ ቅድስና የፀሎት ህይወት በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 13 ላይ እንደተፃፈው በብርቱ ሊፈልጉ ይገባል::

ጥልቅ የሆነ የፀሎት ሕይወት ማጣት ለእግዚአብሔር ቅዱሳን ትልቅ ጉዳት ነው::

ስለዚህ ብርቱ ችግር ሰዎች ብዙ ጊዜ ቢያወሱም ምላሻቸው በየዕለቱ የክርስቶስ ጋር በእምነትና በቃል መመላለስ አልሆነላቸውም እግዚአብሔርንም በሙሉ ልብ አልፈለጉትም::

### ቅዱስ እምቢታ ያስፈልጋል

«በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈፅሙ» (ገላትያ 5÷16):: ይህንን ለመፈፀም ለእግዚአብሔር መገዛት ብቻ ሳይሆን በኃይልና በፅኑነት እግዚአብሔር የሚቆጣጠረው ሕይወት እንዲኖረን ፍላጐቱ ሊኖረን ይገባል::

እግዚአብሔርን በፅኑ ልብ ስንፈልገው ብቻ የተትረፈረፈውን ብቃትና ድል እርሱ ያጐናፅፈናል:: (ማቴዎስ 7÷7)

«ፈልጉ ታገኙማላችሁ» ውድ ወገኖች ሆይ ፊታችሁን ወደ ጌታ መልሳችሁ በመንፈስ መመላለሳችሁ ልባችሁን እስኪሰማው ድረስ በፀሎታችሁ በብርቱ ተዋጉ»

በእግዚአብሔር መንፈስ ድጋፍና አነሳሽነት መንፈሳዊ ሕይወት በሰከነ የድል ሕይወት መምራትና አዳዲሶቹንም ወደ ቤቱ መጥራት ይቻላል።

እኛ ሁላችንም ከቀን ወደቀን በክርስቶስ ወንበር ፊት ወደሚጠብቀን ፍርድ በመፋጠን ላይ እንገኛለን። «ሁላችንም በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን» (ሮሜ 14÷10)

ለድል የሚተጉትን የሚፋለመው ሠይጣን ከመቦዘን ባይቆጠብም በፀሎት ፊልሚያ በመንፈስ በመመላለስ ሕይወታችንን በሚገዛው መንፈስ ቅዱስ በትክክል ድልን መቀዳጀት ይቻላል።

## ከቁጥር የመጉደል አደጋ

«እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ» (ዕብራውያን 4÷1)

ስጋቱ ከእግዚአብሔር ጋር በትጋት ከመሆናችን ሣይሆን ከዳተኛነታችን ከመጉደላችን ነው።

«ወደፊት እፈጥናሁ» (ፊልጵስዮስ 3÷13)

ጌታ እየሱስ ክርስቶስም «በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ» ብሎናል (ሉቃስ 13÷24)

በተግሣፅና ምክሩ መፅሐፍ ቅዱስ እጅግ ተፈላጊውን ሥርዓት የሚያስተምረን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ልባችንና ነፍሳችን ከጌታ በመለየት የሚከተለውን አደጋም ያስጠነቅቀናል።

በእውነት እራሳችንን በመካድ ለራሳችን የሚመቹትን ትተን የጌታን ምሳሌ ተከትለን ለሌሎች ብንኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ በዚህ እንፈፅማለን።

«የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና» (ዮሐንስ 5÷30)።

## ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንገዛ

የእራሳችንን ፈቃድ ብቻ ሳይሆን የምንወዳቸው ሰዎችም ከእግዚአብሔር ዓላማ ፈቃድ ሲያሳዩ ልንፀልይና ልንገስፅ ይገባናል። የንጉስ ሳኦል ልጅና የመዝሙረኛው ንጉስ ዳዊት ሚስት ለጌታ የሚደረግን የተመስጦ ዝማሬ በተቃወመች ጊዜ ንጉስ ዳዊት አልተባበራትም (2ሳሙኤል 6÷12)

አንድ ወንጌላዊ ቁስ ወይም ፓስተር የተገለጠለትን የእግዚአብሔር እውነት ሌላው ያዝንብኛል ብሎ ከማስቀረት የበለጠ አሳዛኝ ጉዳይ የለም። የእግዚአብሔር መልዕክት በሰዎች ይሉኝታ ምክንያት መከልከል የለበትም።

ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ላለማሣዘን የሚጣጣር ሰው መጨረሻው የሀፍረት ሞት እንደሚሆን በካህኑ ኤልና፣ በልጆቹ ሞት ታይቷል። (ሳሙኤል 2÷4)

የሕዝብ መሪዎች ሕዝቡን የሚያስቱበት ጊዜ ሲኖር ትክክለኛ መሪዎች ደግሞ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ሕዝቡን ከስህተትና ጥፋት ያድናሉ። (ኢሳ 9÷16 ገላትያ 1÷19)

«ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ ታዝናላችሁና ታለቅሱማላችሁ» (ሉቃስ 6÷26)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል እግዚአብሔርን ለማስከበርና መንፈስ ቅዱስ በሀይል እንደመጣብን ዓለምን መምሰል ሳይኖርብን በሁሉ ጌታን እያመሰገንን መዳን የሚገኝበትን ወንጌል ብቻ ልንሰብክ ይገባል። (ዮሐንስ 15÷19፣ ሮሜ 12÷2፣ ያዕቆብ 4÷4)

ብዙዎች ታዋቂ የዘመናችን ሰባኪዎች ሰውን ለማስደሰት ሲሉ በሚያቀርቡት ስብከትና ትምህርት ብዙዎችን ወደ ስህተትና ጥፋት በመምራታቸው ከእጃቸው ደም ይፈለጋል ፍርድ አለባቸውና። (ሕዝቅኤል 33÷7) (ምሳሌ 28÷23)

ስለዚህም ዛሬም ዓለማችን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል አንድነት እና ወጥ ሰዎች ንስሐ ገብተው እንዲድኑ በክርስቶስ ፀጋ ተደግፈን እንትጋ። (በወንድም ሙር የምፅአቱ የምሥራች መስራች የተዘጋጀ)

# ከልብ-ጩኸት የመነቃቅት ጉባዔ ላይ የቀረበ መልዕክት (ለመለኮታዊ ጉብኝት ስለመዘጋጀት)

በሪቻርድ ሮበርትስ

በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 72 መጨረሻ ላይ እንዲህ የሚል ድንቅ ቃል ይገኛል፡፡

«ለእኔ ግን ወደእግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» በሕይወቴ ዘመን ሙሉ እጅግ ውድ ከሆኑት ወራቶች የተማርኩት የአስደናቂ ቀናትና ጊዜያት ልምምዴ ወደ እግዚአብሔር የቀረብኩባቸው ወቅቶች ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያን ታሪክ ከእግዚአብሔር ጉብኝት ዘመን የበለጠ መልካም ጊዜ ከቶ የለም፡፡

ይህ ልባችን የሚያቃትትበት ጊዜ ነው አይደለምን? የዚህ ዓይነቱ ጉብኝትስ የምድራችንና የዓለማችን ብርቱ ጉዳይ አይደለምን? ልባችን በአሁኑ ሰዓት ሊሻው የሚፈልግ ነገር የጌታ ጉብኝት ነው፡፡

የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስትን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

«ጢባርዮስ ቄሣርም በነገሠ በአሥራ አምስተኛው ዓመት ጴንጤናዊው ጲላጦስም በይሁዳ ሲገዛ ሄሮድስም በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ ወንድሙ ፊልጶስም በኢጡርያስ ባጥራኮኒዶስም አገር የአራተኛው ክፍል ገዥ ሊሳኒዮስም በሳቢላኒስ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሆነው ሳሉ ሐናና ቀያፋም ሊቀ-ካህናት ሳሉ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ፡፡ በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መፅሐፉ «የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ፤ አዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም የቀና መንገድ ይሁን ሥጋንም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይመልከት» ተብሎ እንደተጻፈ ለኃጢአት ስርየት የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙርያ ወዳለው ሀገር መጣ»

## መጥምቁ ዮሐንስ ልዩነቶችን አሣይቷል

በዚህ የሉቃስ ወንጌል ላይ መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ልዩነትን አስተምሯል፡፡ የመጀመሪያው ልዩነት በክርስቶስና በእርሱ መካከል የነበረውን ሲሆን በዚህም እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ነገር ግን ከእኔ በኋላ የሚመጣው የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል (ሉቃስ 3÷16)

እስኪ የመጥምቁ ዮሐንስን ትህትና አስታውሱ ትህትና እውነትን መካድ ሳይሆን በፈቃደኝነት የራስን ተገቢ ሥፍራና ማንነት መቀበል ነው፡፡ በዘመናችን በቤተክርስቲያን ያለ ዋነኛው ክፉ ነገር ስር የሰደደው ትዕቢት ነው፡፡ ስለራሳችሁ የፈለጋችሁትን ብታስቡም ጌታ ከተነገረላችሁ ውጭ አይደላችሁም «ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም» (ሉቃስ 7÷28) መጥምቁ ዮሐንስ ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ እንደሚልቅ አገልግሎቱም የላቀ ሲሆን ከክርስቶስ አገልግሎት ጋር ግን የሚወዳደር አይደለም፡፡

በእርግጥ እውነትን የበለጠ በተረዳን ቁጥር ትህትናችንም የበለጠ ይሆናል፡፡ እራስን መካብ የትዕቢት ሌላኛው መልክ ሲሆን ከመንገድ የወጣ መታበይ ነው፡፡ እራሳችንን ከምናስበው በታች በማድረግ ለማስመሰል እንጣጣራለን፡፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ዘንድ ግን ማስመሰልና ግብዝነት አልነበሩም፡፡ እርሱ ማን መሆኑን የሚያውቅ ነበር፡፡ ክርስቶስ ማን መሆኑንም አውቋል የክርስቶስን ማንነት በሚገባ በማወቁም እራሱን ዝቅ ለማድረግ በቅቷል፡፡

በዛሬው ዘመን ጥቂቶች ብቻ ለትህትና ሕይወት የቀረቡ ሲሆን በአካባቢያቸው ካለው ጋር እራሳቸውን በማወዳደር ሲኮፈሱ ይስተዋላል፡፡

ለትዕቢትና ለኩራት ብቸኛው መፍትሔ እራሳችንን ከሌሎች ጋር ማወዳደር ሳይሆን የክርስቶስን ተምሳሌት በመፈፀም ላይ ነው፡፡

እራሳችሁ ምንም እንዳልሆናችሁ የምትርቁት ዓይናችሁን በክርስቶስ በአዳኛችን ላይ ስታደርጉ ነው፡፡ የተከበረው እግዚአብሔር አገልጋዮች በመሆን መፅናት የምንችለው እራሳችንን ከደካማው ስጋ ለባሹ ሰው ጋር በማወዳደር ሳይሆን በክርስቶስ መንገድ በመጓዝ ነው፡፡

መፅሐፍ ቅዱሳችንን ለራሳችን በሚመች መንገድ እንተረጉማለን የሚያጋጥመንን ችግርና ሁኔታ በሚጣፍጥ መልክ እንቀበለዋለን፡፡ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ተረድተን በቅዱስ ቃሉ የምንቃናውና የምንባረከው የልቦናችንን ዓይን በእግዚአብሔር ላይ ስናደርግ ብቻ ነው፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ እንዲህ ታላቅ አገልጋይ ሊባል የበቃው በፍፁም ትህትና ዓይኖቹን ከጌታ በማንሳቱ ነበር፡፡ የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት በጥምቀቱም ሆነ በአገልግሎቱ እራሱን ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በታች ማድረጉ ለእኛ ምሳሌ ነው፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ብዙዎችን ወደ ጌታ መመለሱ፣ የጌታን መንገድ ጠራጊ መሆኑ፣ ያለመታዘዝን በመታዘዝ ማስቀየሩ፣ ሰዎችን ለጌታ ማዘጋጀቱ የቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ስራ ነው፡፡

ዛሬ በሚሊዮኖች የማቆጠሩ ክርስቲያኖች ከአሳሳች አስተማሪዎቻቸው የተነሳ ክርስትናን የጤናና የሀብት ማስገኛ ብቻ አድርገው ዋናውን የኃጢአት ይቅርታንና የዘላለም ሕይወትን ዓላማ የዘነጉ ይገኛሉ፡፡ በኃጢአት መኖርን እየወደዱ ከገሃነም መትረፍን ማሰብ አይቻልም፤ ሁለት መንገድ በክርስትና የለም ሕይወት ወይም ሞት፣ ክርስቶስ ወይም ሰይጣን፡፡

## የንስሐ ፍሬን ስለማፍራት

«እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ (ሉቃስ 3÷8)»

በህይወታችን የንስሐ ፍሬ ለመገኘቱ ምን ያህል ግድ ይላችኋል? አንድ ሰው ይህንን ጥቅስ በቸልታ ካነበበው አጠቃላይን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር መምጣት ዓላማ የዘነጋ ይሆናል፡፡ ለመጥምቁ ዮሐንስም ሆነ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክት እምቢተኛ ሆነው ያልተጠመቁት ግብዝ ፈሪሳዊያንና መሰሎቻቸው ብቻ ሲሆኑ ብዙዎች ልባቸው በቃሉ ስለተነካ ተጠምቀው እግዚአብሔርን የሚያከብር ሕይወትን መለማመድ ጀምረዋል፡፡

ዛሬም በየአብያተክርስቲያናቱ በየከተማውና በየመንደሩ እንዲሁ ነው፡፡ ክርስቶስን አምነው በንስሐ ፍሬ የሚመላለሱና ክርስቶስን እምቢ ብለው ያለፍሬ የቀሩ ወይም የስጋ ስራ የተገለጠባቸው አሉ፡፡ በማንኛውም ስብከትና አምልኮ የኑዛዜ ጊዜ ሊኖር የተገባ ሲሆን በዚህም ሰዎች በየዕለቱ የኃጢአት ይቅርታን ከእግዚአብሔር ሊቀበሉና ሊታደሱ የንስሐ ፍሬም ሊያፈሩ የግድ ነው፡፡ እርሱ የክርስቶስ መንፈስ ይህን ያደርጋልና»

እግዚአብሔርን በፀጋና በስጦታው ማገልገል እንዲቻል ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሊገኙ ያስፈልጋል፡፡ (ገላትያ 5÷21) እግዚአብሔርም ከክፉ ልብ የሚወጣን ፀሎት አይሰማም (መዝሙር 65÷18)፡፡ ሰዎችን ለእግዚአብሔር መንግስት ማዘጋጀት የሚቻለው በቅዱስ ቃሉና በፀጋው ብቻ ሲሆን ያንን ለመፈፀምም በንፁህ ትምህርት በመመራት ኃጢአትን በመራቅ በፀሎት ወደጌታ በመቅረብ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቤት ጌታ እንዳስተማረው የሌላ የምንም ድርጊት መፈፀሚያ ሳይሆን የፀሎት ቤት ነውና (ኢሳያስ 6÷7 ማቴ 21÷13)

ቤተክርስቲያን የቅዱሳን ጉባዔ፤ በክርስቶስ ያመኑት ማህበርና ቃሉና ፀጋው የሚሰጥባቸው ስፍራና ህብረት ሲሆን መሠረቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልና ኢየሱስ ክርቶስ ብቻ ነው፡፡ «በዓለት ላይ ስለተመሠረተ አልወደቀም» መሠረት የለም እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ቆርንቶስ 3÷11)

# አመስጋኝነት እና ትህትና

*በዴቭ ቡትስ*

ክርስቲያኖች ከሚገነዘቡት እጅግ የበለጠ ውጤት በአመስጋኝነት ይከሰታል። መፅሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እንድናመሰግን በሚያሳስቡ አያሌ ምዕራፎችና ጥቅሶች የተሞላ ነው።

ከእነዚህ በመቶዎች ከሚቆጠሩት የምስጋና ጥቅሶች አመስጋኝነት ላይ የሚያተኩሩትን ብቻ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን።

«ስለዚህ የማይናወጥን መንግስት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ፀጋ እንያዝ» (ዕብራዊያን 12÷28)

«በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ» (ቆላስያስ 3÷15)። ከማመስገን ጋር በፀሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ» (ቆላስያስ 4÷2) «እግዚአብሄርን አመስግኑ፣ ስሙንም ጥሩ» (1ዜና 16÷8) «በዚያም ቀን እንዲህ ትላላችሁ፣ እግዚአብሄርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ በአህዛብ መካከል ሥራውን አስታውቁ ስሙ ከፍ ያለ እንደሆነ ተናገሩ» (ኢሳይያስ 12÷4)

## እግዚአብሔርን ባለማመስገናችን ምን ይከተላል?

በመፅሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔርን ባለማምለክ የሚከተለውን የሚያሳስብ አንድ ብርቱ ቃል ይገኛል። «እግዚአብሔርን እያወቁ እንደእግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ። ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የሚያስተውለውም ልባቸው ጨለመ (ሮሜ 1÷21) በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ እንደፃፈልን ያለማመስገን በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ እንደሆነና የዚህም ሃጢያት ክፉ ውጤት እንዳለ ነው። እግዚአብሔርን ያለማመስገን ከእግዚአብሔር የመለየት ጅማሬ ነው።

## የትህትና ቁልፍ

አመስጋኝነት ለተግባራዊ የክርስትና ሕይወት እጅግ አስፈላጊ የሆነ የትህትና ቁልፍ ነው። ሰዎች በየምክንያቱ ለሚሰጡን ስጦታና ግብዣ የምናመሰግነውን ያህል ሁሌም ለሚሰጠን እግዚአብሔር ማመስገን ምንኛ ያስፈልግ! በእውነተኛ ትህትና የእግዚአብሔር ጉብኝት ሲኖር ትህትና በጐደለው ሕይወት አንዳች መንፈሳዊና ክርስቲያናዊ እድገት አይገኝም። ትዕቢት እግዚአብሄርን ከዙፋኑ ለማውረድ ስለሚጣጣር በመልካም ትህትና ልንፋለመው ያሻል። ትዕቢትን ለማስወገድ እራሳችንን በመጣል በመጥፎ ስሜት በመሞላት ለማስወገድ እንጣጣራለን። ይህ ትግል ደግሞ ማለቂያ የሌለው ፍልሚያ ነው።

ከዚህ የበለጠው የትህትና መንገድ ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ መታመን ነው። ሰዎችን ለጥሩ ውለታቸው እናመሰግናለን እንደምንል ሁሉ ለእግዚአብሄርም ዘወትር የከፈሮቻችንን የምስጋና ፍሬ እናቅርብ። (ዕብ 13÷15)

## የትህትና ፀጋ

ትህትና የነፍስ ትፍስህት እና የመንፈሳዊነት መሠረት ሲሆን ለበጐ ምግባር ከእግዚአብሔር የሚገኝ ፀጋ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን በሕይወቱ ዘመን ሊያጣው የማይገባ ዋነኛ ነገር ትህትና ነው።

በእግዚአብሄር ፊት እራሳችንን በትህትና ባዋረድን ቁጥር ትህትና ለህይወታችን እጅግ ተፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን።

ትዕቢትን የመሰለ በተፈጥሯችን ስር በመስደድ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሰው ዘር ጋር ያለንን በጐ ልዩነት የሚባል የለም። በዚህች ምድር ላይ በሁላችን ዘንድ ስር ሰድዶ ድካማችንን፣ ጉዞችንና

ትዳራችን የሚበላ እርም እየፈለቀብን መሆኑን አላስተዋልንም።

ትዕቢት ሊቀ መልአክ የነበረውን ሰይጣንን ቁልቁል ያስወረደ ሲሆን ለእኛም ከሰማይ ከዚሁ ፍንጣቂ በስጋ ስራ እንዳንገኝ በትህትና ኑሮ ወደ ጌታ እንቅረብ።

## እግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈሱን ስንጠይቀው ይሞላብናል

*(በአንድሪው ሙሬ)*

«እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው!» (ሉቃስ 11÷13)

ክርስቶስ ያዘዘን እንድንጠይቅና እንድንቀበል ሲሆን እግዚአብሔርም ያለማቋርጥ ለጥያቄያችን መልስ የሚሰጥ ነው። የምድራዊ አባት ለልጁ እንጀራ እንደሚሰጥ ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሱን ለሚጠይቁለት ሁሉ ይሰጣል።

የመንፈስ ቅዱስ አሠራር በአጠቃላይ በአንድ መርህ ላይ ይመራል እርሱም ከጌታ በመጠየቅና በመቀበል ላይ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኞች ላይ የሚወርደውና ከእነሱም እየወጣ ሌሎችንም የሚባርከው እንደፈሳሽ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ተትረፍርፎ ለሌሎች መፍሰስ የሚከናወነው ጠይቁ ታገኙማላችሁ በሚለው መለኮታዊ ቃል መሰረት ነው።

በእግዚአብሔር የማዳን ስራ ውስጥ ፀሎት ከፍተኛ ሥፍራ የሚኖረው እግዚአብሔር ከእርሱ እንድንቀበል ያዘጋጀው መንገድ በመሆኑ ነው።

የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን በበአለሃምሳው ወይም በጰንጤ ቆስጤ ዕለት መመሥረት የተካሄደው በእግዚአብሔር መንፈስ መውረድና በአማኞች ላይ በመፍሰስ ነው። በዚያውም መንፈስ ሁሉም አማኞች አንድ ሆነው ሲግባቡ ሦስት ሽዎችም ወደእግዚአብሄር መንግሥት ተጨምረዋል። በዚያው መንፈስም ቤተክርስቲያን ቃሉን ጠብቃ ለእኛ ዘመን በቅታለች (ሐዋርያት 2:1-4)

ከሰይጣን መንጋጋ ሕዝቡን እግዚአብሔር የሚቤዠውም በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን ለዚህ ልዩ ስራም እግዚአብሔር ሕዝቡን በፀሎት እንዲተጉና ይህን መፈፀም የሚያስችለውን መንፈስ ቅዱስን እንዲጠይቁ አሳስቧል።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለክርስቶስ መመስከር እንዲያቆሙ በሸንጎ ተከሰው በቀረቡበት ወቅትም ስለጌታ ከመናገር እንደማይቆጠቡ እንዲናገሩ ያስቻላቸው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን በብርቱ ንግግራቸውም አያሌዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነክተው በክርስቶስ አምነዋል።

በሐዋርያቱ ሥራ በስድስተኛው ምዕራፍ ሐዋርያቱ አበክረው የተናገሩት ጉዳይ እራሳቸውን ለፀሎትና ለእግዚአብሔር ቃል አሳልፈው መስጠታቸውን ነው።

በምድራችን ለሚካሄድ ማንኛውም መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የወንጌል ማዳረስም ሆነ ሰብአዊ እርዳታዎች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉና በቅዱስ መንፈሱ እግዚአብሔር ሰዎችን ሲነካ ብቻ ነው። ይህ በጐ ተግባርም ከክርስቶስ ፀጋ የተነሳ በሰዎች ዘንድ እንደሚታይና ይህ የትክክለኛ ሃይማኖት መግለጫ መሆኑን ሐዋርያው ያዕቆብ በመልዕክቱ ፅፏል (ያዕቆብ 1 ÷ 27)።

በእግዚአብሔር ቤት በቤተክርስቲያን በአማኞች ጉባዔና ማህበረ ምእመናን ብዙ ልዩ ልዩ በጐና ቅዱስ ተግባራት ሲኖሩ የሁሉም መልካም እንቅስቃሴ አንቀሳቃሽ መንፈስ ቅዱስ ጌታ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ነው። (1 ቆሮንቶስ 12)።

# ከክርስቶስ መስቀል አትራቁ!

እራሱን ለእግዚአብሔር ሊቀድስ የሚፈልግ ክርስቲያን ከክርስቶስ መስቀል ስር ሊርቅ አይገባውም። መስቀሉ የእግዚአብሔር ሀይል ምስጢር የሚገለጥበት ድልም የሚገኝበት መንገድ ነው።

መስቀሉ የክርስቶስ መከራና ስቃይ ለሰው ዘር በደልና ኃጢአት ማስተሰርያ (ማስወገጃ) የተካሄደበት የክርስትና እምብርት ክንዋኔ ነው።

በመስቀሉ ቃልና መንፈስ ክርስቲያኖች የጨለማውን የሰይጣን መንግስት በማፈራረስ የታሰሩትን ምርኮ የሚወስዱበትና ለክርስቶስ የብርሃን መንግስት የሚያበቁበት ሀይል የሚገኝበት ነው።

መልካሙን ገድል መፈፀም በውጊያ መፅናት እና መቆም የሚገኘው በመስቀሉ ቃል ነው። (ኤፌሶን 6÷12፤ 2ጢሞቲዎስ 4÷7)

ከክርስቶስ መስቀል ስር መሆን ማለት ክርስቶስን ለመምሰል መጣጣርን ዓለምንና ስራዋን መካድና ለስጋ ስራዎች ለክፋቱና ምኞቱ ያለመገዛት ነው። መስቀሉን የሚወዱ የስጋ ምኞት አይገዛቸውም (ሮሜ 15÷3)

በመስቀሉ ላይ ክርስቶስ የተዋረደና የተሸነፈ ቢመስልም እርሱ በትክክል የከበረበትና ሠይጣንን ያሸነፈበት የእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈፀመበትን ታላቅ ሥራ አጠናቅቆ «ተፈፀመ» ብሏል (ዮሐንስ 19÷30)

ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ 2÷20 ላይ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔ አሁን አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል ብሎ ያስተማረን እኛም በእምነት ከክርስቶስ ጋር በቃልና በሥራ እንድንስማማና የእኛ የስጋ ፈቃድ በሥራ እንድንስማማና የእኛ የስጋ ፈቃድ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ እንዲፈፀምብን ነው።

ከክርስቶስ መስቀል ስር መሆን ለስጋ ሀሣብና ለዓለም ትርኪምርኪ መሞትና በክርስቶስ ግን ሕያው መሆን ነው (ቆላስያስ 3÷3)

ክርስቶስ ለኃጢአታችን በመሞት ሞትን አሸንፎ በትንሳዔ እንደተነሳ ሁሉ እኛም በክርስቶስ መንፈስ ለስጋ ሀሣብና ፈቃድ ሞትን በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ሆነን ለዘላለም ከጌታ ጋር እንኖራለን (ሮሜ 14÷9)

ስለወንጌልና በክርስቶስ ኢየሱስ ስለሚገኘው የኃጢአት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ማሰብና መኖር የሚቻለው በክርስቶስ ሞት በመከራውና በስቃዩ የተገኘ ልንን ድል በእምነት በመቀበል ነው።

ከዚህ ዓለም ክፉ ምኞት ከሰጋ ስራና ከሰይጣናዊ ድርጊቶች እራሳችንን በክርስቶስ ደም ማንፃት የምንችለው ሁለንተናችንን በክርስቶስ መስቀል ስር ስናስገዛና የመስቀሉ መልእክትና ቃል ሲዋሀደን፣ ሲገዛን፣ ሲሞላብን ነው።

የኃጢአት ይቅርታን ከእግዚአብሄር በክርስቶስ መቀበልና በመንፈስ ቅዱስ የበረከት ሕይወትን መቀጠር የምንችለው የክርቶስ መስቀልን ስንሸከምና አብረነው ስንጓዝ ነው።

ጌታ ሊከተለኝ የሚፈልግ መስቀሉን ተሸክሞ በየእለቱ ይጓዝ ያለው ከእርሱ ቃል ሳንለይ ለዓለምና ለሰይጣን ሳንገዛ ስጋችን ሳይጐትተን እንድንመለስና እራሳችንን እንድንክድ ነው (ሉቃስ 9÷23)።

የዓለም ትምህርትና የአንዳንዶቹ በክርስትና ስም የሚሸነግሉ «የሌላ ወንጌል» አስተማሪዎቹ ስብከት «እራሳችሁን ውደዱ» «በእራሳችሁ ችሎታ» «በእራሳችሁ ውሳኔ» ትድናላችሁ የሚል እኔነትንና የሰውን ስራ የሚያሞጋግስ ሲሆን ጌታ ግን ከነሐዋርያቱ ያሉት «እራሳችሁን ካዱ» «በእራሴ በጐነት የሌለኝ ለሞት የተሰጠሁ» እንድንል ነው።

ማንኛውም ክርስቲያን በእራሱ ብቃትና ሀይል ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል እንደማይችል፤ በተፈጥሮው ለክፋት እንደሚሸነፍ ከላይ ከእግዚአብሔር ብቻ እርዳታ እንደሚያስፈልገው እስካላመነ ድረስ አሁንም ገና የመስቀሉ ምስጢር ያልገባው ነው።

«ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን» እውነትም በእኛ ውስጥ የለም ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢያታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነ ፃድቅ ነው። (1 ዮሐንስ 1÷9)

## መስቀላችንን ስለመሸከም

ልንሸከም የሚገባ መስቀል እንደሚኖር ጌታ በቃሉ ያረጋገጠልን ሲሆን ይህም መስቀል የክርስቶስ ሳይሆን የእራሳችን ነው። ለእያንዳንዳችንም ይህ መስቀል ክርስቶስን አምነን መጓዝ ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ተሠጥቶናል። ጌታ በትክክል በቅዱስ ቃሉ እንዳስተማረን ልንከተለው ብንወድ እራሳችንን ክዳን የየራሳችን መስቀል እንድንሸከም የግድ ነው። (ማቴዎስ 16÷24)

በየዕለቱ መስቀላችንን ተሸክመን መጓዛችን ከየዕለቱ የክርስትና ኃላፊነታችንና ለክርስቶስ ስንል ከምንከፍለው ዋጋና መስዋዕትነት ጋር የተቆራኘ ነው። ይህ መስቀላችን ለመዳናችን የምናደርገው ሳይሆን ስለዳንን የሚጠበቅብን ኃላፊነት ነው። እራስን ከፍ ማድረግ ከሰዎች ሙገሣ መጠበቅ ዝናና ከበሬታ ከመስቀላችን ጋር አይሄድም።

ያለመስቀል ክርስትና ትርጉም የለሽ ሲሆን የዘመኑ እውቅ ተብዬ ሠባኪዎችም መስቀላቸውን በመጣል ከክርስቶስ ፀሮች ጋር መደራደርና መጣመሩን ተያይዘውታል።

ክርስቲያን አንድ ነገር እያስተዋለ ቢቻለው ከሁለም ጋር በሰላም ሊኖር ይገባዋል እንጂ ለሰላም ሲል፣ ለመከበር ሲል፣ ለመወደድ ሲል መስቀሉን በመጣል የተለሣለሰ ኑሮ እንዲኖር ፈፅሞ አልተጠራም።

እኝህ የሀብት እና የደስታ ወንጌል ሰባኪዎች በምዕራቡ ዓለም፣ በሀገራችን ኢትዮጵያም ጭምር ስተው የሚያስቱት መስቀላቸውን አሽቀንጥረው የጣሉ ናቸውና ከትምህርታቸውና ከህብረታቸው እንራቅ! ጌታኮ እራሱን ለማስደሰት አልኖረም (ሮሜ 15÷3) ለስማችን ለዝናችንና ለጥቅማችን የምንሮጥ ከሆነ የተሰቀለውን ክርስቶስን መምሰላችን የትኣለ? ከክርስቶስ ጋር የተሰቀልንበት መስቀልና የየግላችን መስቀል የተለያዩ ቢሆኑም ሁለቱም ወደ አንድ አቅጣጫ ያመሩናል። እርሱም ለበደላችን በመስቀል የተሰቃየውና የሞተው ክርስቶስን በየዕለቱ መስቀላችንን ይዘን ስንከተለው የሚረዳን ክርስቶስ በመፅሐፍ ቅዱሳችን የተገለጡት የእምነት አባቶች ጌታ ክርስቶስም ጭምር የእያንዳንዳቸው መስቀል ነበራቸው። መስቀላቸውንም በፅናት ተሸክመው በመጓዝ ሕይወታቸውን በድል ፈፅመዋል። አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ኤልያስ፣ ጳውሎስና ሐዋርያቱ ሁሉም ዝናቸውን፣ ክብራቸውን ጥቅማቸውን ለክርስቶስ ሲሉ ትተው መስቀላቸውን ተሸክመው ተጉዘዋል። እኛም እንዲሁ በክርስቶስ እንጓዛለን።

## ቤተሰባችንና ቤታችን ለእግዚአብሔር ስለማቅረብ

ቤተሰባችንና ቤታችንን፤ ከእግዚአብሔር የተሰጡትን እነርሱን ለማስከበር አስቀድመን ልንከባከባቸው የሚገቡ ስጦታዎቻችን ናቸው።

በተለይም በእግዚአብሔር ቤት አገለግላለሁ የሚል ሰው የእራሱን ቤተሰብ በሚገባ ሳይመራ ይህን ትልቅ ኃላፊነት መረከብ እንደማይችል የእግዚአብሔር ቃል ያሳስባል። (1ጢሞ 3÷5)

በእርግጥ የዘመኑ የኑሮ ሩጫና ውድድር ለቤተሰብ ሊሰጥ የተገባውን ጊዜና ድጋፍ የሚሻማ ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል ሳይለወጥ እንደማያሳስበን ለቤተሰባችን ተገቢውን ማድረግ እንደሚገባን ዛሬም ያሳስበናል።

ለመንፈሳዊ ሕይወትና ውጊያ የየራሳችን ቤተሰብና ቤት ለእግዚአብሔር ቃልና ለፀሎት መነሻ ቅድሚያ ሥፍራችን ሲሆን በቤተሰባችን የእራሳችን ቤት የማንፈፅመውን የቅድስናና የትህትና ኑሮ ብንሰብክ ወይም ብናስተምር ከንቱ ግብዝነትና ኃጢአትም ነው።

ጠንካራ ማህበረ-ምእመናንና ቤተክርስቲያን፣ ጠንካራ ማህበረሰብና ሀገር የሚገኙት ጠንካራ ቤተሰባዊ ፍቅርና መረዳዳት መሠረት ከሆነባቸው ከክርስቲያናዊ ቤተሰቦች ነው።

የዘመናችን የሞራል ውድቀት፣ የዝሙት መስፋፋት፣ ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱና በፍች የሚማቅቁ ህፃናት መበርከት የሚከተለው ለቤተሰብ

ጌታ በቅዱስ ቃለ የሰጠው መመሪያ ባለመተግበሩና ይልቁንም በተፃራሪው በመካሄዱና በመሰበኩ ነው።።

እግዚአብሄር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንድንጠይቅና እንድንቀበል የሰጠን ትዕዛዝና የተስፋ ቃል ለቤተሰባችንም ይሰራል።።

## ለቤተሰብና ለቤታችን የሚረዱ ነጥቦች

### በረከት

ወላጆች እርስ በእርሳችሁም ሆነ ልጆቻችሁን ጌታ እንዳደረገው ባርኩዋቸው፣ መርቁዋቸው (ማርቆስ 10÷16) «አቀፋቸውም፣ እጁንም ጭኖ ባረካቸው» «እግዚአብሄር ይባርካችሁ፣ ይጠብቃችሁ፣ እግዚአብሄር ፊቱን ያብራላችሁ፣ ይራላላችሁ፣ እግዚአብሄር ፊቱን ወደ እናንተ ያንሳ ሰላሙንም ይሰጣችሁ» (ዘኅልቆ 6÷24)።።

እግዚአብሔር ነፍስን፣ ስጋንና መንፈስን ሙሉውን ሰው የፈጠረ አምላክ ሙሉውን ሰው እንደሚባርክ እኛም የቤተሰባችን ነፍስ፣ መንፈስና ስጋ እንዲጠበቅና እንዲባረክ እንፀልይ።።

«የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታች ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ» (ተሰሎንቄ 5÷23)

## የሰላምና የተሰፋ ፀሎት

እግዚአብሔር አባት ሆይ ይህን በሚያነቡ ሁሉ ላይ ቅዱስ መንፈስህ ይለቀቅላቸው።። ስለምትሰጣቸውም ሰላም ስምህ ይከበር (መዝሙር 29÷11)

የተስፋ አምላክ እግዚአብሔር አንተ ለሚጠሩህ የምትደርስ ብርታትንም የምታሟላ ሁሉን ቻይ ጌታ ነህና ከእነዚህ በረከቶች ይህንን ለሚያነቡ ከነመላው ቤተሰባቸው አድርግላቸው (ሮሜ 8÷14)

ያለነቀፋም በክርስቶስ ደም ነፅተን እንድንገኝ ቅዱስ መንፈስ ይመላብን፣ ይቀድሰን አሜን።።

# ዓለም ዓቀፍ የፀሎት ርዕሶችና ዘገባዎች

### ሁከትና ሽብር እንዲቆም እንፀልይ

በዓለማችን በአሁኑ ጊዜ ሁከትና ሽብር እጅግ በአስጊ ሁኔታ ሰፍኖ የሚገኝ ሲሆን ኃላፊነት የጐደላቸው እንደ ኢራን፣ ኮርያ ያሉ መንግስታት አውዳሚ መሣሪያዎችን ሊያመርቱ ይንቀሳቀሳሉ።።

በአውሮፓ የሙስሊም አክራሪዎችና ተከታዮች ቁጥር በመጨመር ላይ ሲሆን በኢራቅ፣ በአፍጋኒስታን፣ በሶማሊያና በሰሜን አፍሪካ የአሸባሪ ሙስሊሞች ስጋት ከመቼውም በበለጠ አሳሳቢ ሆኗል።።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም አለቃ በእነዚህ ሥፍራዎች በልጆቹ አማካኝነት ሰላሙን እንዲልክ በማንኛውም አቅጣጫ የሚደረግ የጥፋት ዕቅድ እንዲፈርስ በብርቱ እንፀልይ።።

### የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ስራ በሕንድ

ትኩረት ለወላጆች የተሰኘ የሚሲዮናዊ ድርጅት በሕንድ ሀገር ለሚገኙ አያሌ ቋንቋዎች መፅሐፍ ቅዱስን ተርጉሞ ለማቅረብ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛ ል።። በሕንድ 430 የሚጠጉ ቋንቋዎች ሲገኙ 60 ብቻ መፅሐፍ ቅዱስ ተተርጉሞላቸዋል።።

እየተሻሻሉ በመጣው የሕንድ የቋንቋ ዕድገት መሠረት የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ስራው እንዲሳካ ብዙ ሚሊዮኖች ክርስቶስን ለማያውቁበት በልዩ ልዩ ምትሐታዊ ሃይማኖት ለተያዘች ሕንድ እንፀልይ።።

### በማረሚያ ቤቶች ለሚገኝ አገልግሎት እንማልድ

በዓለም ዙሪያ ሀገራችን ኢትዮጵያም ጭምር በማረሚያ ቤቶች ለሚካሄድ የወንጌል ማዳረስ

አገልግሎት በፀሎትና በመፅሐፍ ቅዱሳት ስጦታ እንትጋ። የታሰረ ወዳጅ ዘመድ ካለን ዛሬውኑ መፅሐፍ ቅዱስ እናበርክትለት። በአሜሪካ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ታራሚዎች መፅሐፍ ቅዱስ አግኝተዋል፤ ጌታን ለዚህ እናመስግን።

## አጭር የመዳን ምክሮች

### እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?

1. በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተም ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ (ሐዋርያት 16÷31)
2. ሕይወታችን እንዲስተካከልና እንዲታደስ ኃጢያታችንን በመናዘዝ ንስኃ እንግባ (ሮሜ 3÷23 6÷23 ኢሳይያስ 55÷7)
3. ለኃጢአታችን የተሰቃየውን፣ የሞተውንና በሶስተኛው ቀን ሞትን አሸንፎ የተነሳውን ክርስቶስን እንመን፣ እንታዘዝ (ማርቆስ 10÷33 ዮሐንስ 1÷12)

## ማሳሰቢያ

በየጊዜው ለምትልኩልን የፀሎት፣ የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ ሁላችሁንም በዚህ አጋጣሚ እናመሰግናለን።

አሁንም ለአገልግሎቱ መቀጠል በብርቱ የሚያስፈልገንን ፀሎት፣ ምክርና የገንዘብ እርዳታ ቀጥሎ ባለው አድራሻ በመላክ ከእኛ ጋር የእግዚአብሔርን መንግስት እናስፋፋ።

***ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው።***


**የምፅአቱ የምሥራች**

*የወንጌል መነቃቃት የትርጉም አገልግሎት*
*ትርጉምና ቅንብር፦ አደፍርስ ሀብቴ መካሻ*
*አሳታሚ፦ ሪክ ካርማይል*
*አርትኦ እና ዲዛይን፦ ኤልሣቤጥ ባሰልዮስ*
*አስተባባሪ፦ ፋንታዬ ግርማ*
*አማካሪ፦ ሠፋኒት አክሊሉ*
*በወንጌል አማኞች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚካሄድና*
*ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግል የወንጌል አገልግሎት።*
*የስልክ ቁጥር 190612*
*የ.ፓ.ሣ.ቁ 8986*
*አዲስ አበባ*
*ኢትዮጵያ*